## የመመረቂያ ዱካ

# በ 2025 ከሚመረቁ ክፍሎች ጀምሮ

### ዘጠነኛ ክፍል የመጀመሪያ ዓመት፡- 2021–2022

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የመመረቂያ መስፈርቶች በአጭሩ

**የሜሪላንድ ስቴት 1 ዲፕሎማ ይሰጣል። ይህም የሚከናወነው** ለሁሉም የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ምሩቃን አራት መስፈርቶችን በተሳካ ሁኔታ በማሟላት ላይ በመመሥረት ነው። እነዚህም፡- ምዝገባ፣ የኮርስ ክሬዲት፣ የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) እና የሜሪላንድ መመዘኛዎችን በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቅ ናቸው። ተማሪዎች የምዝገባ ተፈላጊ መስፈርት በማሟላት ከ 8ኛ ክፍል ባሻገር አራት አመት በሚያመረቃ ሁኔታ መፈፀም አለባቸው። ሌሎች ተፈላጊ መስፈርቶች በሙሉ ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ ባጭሩ ተገልፀዋል። ስለ 2021-2022 እባክዎ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ኦንላይን የ "ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የኮርስ መግለጫ መጽሔት" በዚህ በይነመረብ ላይ ይመልከቱ coursebulletin.montgomeryschoolsmd.org/Home/PlanningTools ወይም የበለጠ መረጃ ለማግኘት የት/ቤትዎን ካውንስለር ያነጋግሩ።

<table>
<tr><th colspan="3">የኮርስ ክሬዲቶች</th></tr>
<tr><td>እንግሊዘኛ</td><td colspan="2">4 ክሬዲቶች</td></tr>
<tr><td>ኪነ-ጥበባት</td><td colspan="2">1 ክሬዲት የተመደበ ለ FA በኪነጥበብ (አርት)፣ ዳንስ፣ ድራማ/ቲያትር፣ እና ሙዚቃ FAበኮርስ መግለጫ መጽሔት ላይ የተገለጸውን መስፈርት የሚያሟላ።</td></tr>
<tr><td>የጤና ትምህርት</td><td colspan="2">1 ክሬዲት</td></tr>
<tr><td>ሂሳብ</td><td colspan="2">4 ክሬዲቶች፣ ከሜሪላንድ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአልጀብራ ፈተና ጋር የሚመጥን 1 የአልጀብራ ትምህርት ወይም አልጀብራ I ቅድመሁኔታ የሆነበት ተከታታይ የሒሳብ ኮርሶች 1 ወይም ከዚያ የበለጠ ክሬዲቶችን፣ እና ደረጃ የጠበቀ የጂኦሜትሪ ይዘት ጋር የሚመዘዘን 1 የጂኦሜትሪ ትምህርት።<br><br>በ 2018 እና ከዚያ በኋላ ለሚመረቁ ተማሪዎች የስቴት መስፈርቶች። በ 2018 እና ከዚያ በኋላ የሚመረቁ ተማሪዎች በያንዳንዱ የሁለተኛ ደረጃ ዓመት የሂሳብ ኮርስ መውሰድ አለባቸው። ይህ ለተማሪዎች መመሪቂያ በሂሳብ ከ 4 ክሬዲቶች በላይ ሊያስገኝላቸው ይችላል።</td></tr>
<tr><td>የሰዉነት ማጎልመሻ ትምህርት</td><td colspan="2">1 ክሬዲት</td></tr>
<tr><td>ሳይንስ</td><td colspan="2">3 ነክስት ጀነሬሽን ሳይንስ ስታንዳርድስ (NGSS) ክሬዲቶች፣ 1 የስነ-ህይወት ሳይንስ ክሬዲት ከሜሪላንድ የስነ-ህይወት ሳይንስ ጋር የተቀናጀ የሳይንስ ፈተና፣ 1 የፊዚካል ሳይንስ ክሬዲት፣ እና 1 ክሬዲት በስነ-ምድር/ህዋ ሳይንስ ወይም ከስነ-ምድር/ህዋ ሳይንስ ርእሶች ጋር የተቀናጀ NGSS ኮርስ።</td></tr>
<tr><td>የህብረተሰብ ሳይንስ ጥናት</td><td colspan="2">3 ክሬዲቶች፣ 1 የአሜሪካ ታሪክ ክሬዲት፣ 1 የዓለም ታሪክ ክሬዲት፣ እና 1 የብሔራዊ፣ የስቴት እና የአካባቢ ስነ-መንግስት ክሬዲት ያስፈልጋል።</td></tr>
<tr><td>የቴክኖሎጂ ትምህርት (TE)</td><td colspan="2">1 ክሬዲት ለ..የተመደበTE። ይህን መስፈርት ለማሟላት የተመደቡ ኮርሶች በኮርስ መጽሔት ላይ ተገልጸዋል። አድቫንስድ ቴክኖሎጂ (AT) ኮርሶች የ TE ኮርስ መስፈርቶችን አያሟሉም።</td></tr>
<tr><td>ዎርልድ ላንጉጀስ ወይም ጥናት የሚደረግበት ፕሮግራም እና ተመራጮች</td><td>2 ክሬዲቶች በተመሳሳይ ዎርልድ ላንጉጅ እና 2 ክሬዲቶች በተመረጡ ኮርሶች ወይም</td><td>ስቴት ያፀደቀው የጥናት ፕሮግራም (POS) ማጠናቀቅ እና ቢያንስ 0.5 ክሬዲት በተመራጭ ኮርሶች ወይም ከዚያ የበለጠ በ POS ሁኔታ ላይ የተመሠረተ</td></tr>
<tr><th colspan="3">የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL)</th></tr>
<tr><td>የተማሪ የአገልግሎት ትምህርት (SSL)</td><td colspan="2">75 የአገልግሎት-ትምህርት ሰአቶች<br>ከ 6ኛ ክፍል በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ MCPS ለሚገቡ ተማሪዎች የ SSL መስፈርት በተመዘዘኘ ይያዛል።</td></tr>
<tr><th colspan="3">የሜሪላንድ ሁለገብ አጠቃላይ የምዘና (ፈተና) ፕሮግራም (MCAP)<br>የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምዘና (HSA) መስፈርቶች [1,2,3]<br>እነዚህ የምዘና መስፈርቶች በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት (MSDE) አማካይነት ሊለወጡ ይችላሉ።</th></tr>
<tr><td>አልጀብራ 1</td><td colspan="2">በአልጀብራ 1 የተገኘ የኮርስ ክሬዲት እና<br>• ከ 2019-2020 በፊት የአልጀብራ 1 ፈተና/ምዘና ማለፍ፣ ወይም<br>• የአልጀብራ 1 ምዘና/ፈተና መውሰድ<br>• በ 2019-2020 የአልጀብራ 1 ኮርስ ያለፈ(ች) ከሆነ፣ ማሟላት የሚጠበቅበ(ባ)ት የኮቪድ ምርመራ መስፈርት እንዲቀር ተደርጓል። ምንም ተጨማሪ የምርመራ ተሳትፎ ማድረግ አያስፈልግም እና የተማሪው(ዋ) የምርመራ ሁኔታ "አስፈላጊ አይደለም" ተብሎ ይነበባል።</td></tr>
<tr><td>እንግሊዝኛ 10</td><td colspan="2">እንግሊዝኛ 10 ወይም ተመጣጣኝ በሆነ ኮርስ የተገኘ ክሬዲት፣ ወይም እንግሊዝኛ 10 ለ ELs የተገኘ የኮርስ ክሬዲት እና<br>• የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስነጥበብ/ሊተርሲ ፈተና (ምዘና) መውሰድ</td></tr>
<tr><td>ስነመንግስት</td><td colspan="2">ብሔራዊ፣ ስቴት፣ እና የአካባቢ ስነመንግስት ወይም ተመጣጣኝ በሆነ ኮርስ የተገኘ ክሬዲት እና<br>• ስለ ስነ-መንግስት ምዘና/ፈተና መውሰድ</td></tr>
<tr><td>ሳይንስ</td><td colspan="2">በባዮሎጂ ወይም በሌላ ተመጣጣኝ ኮርስ የተገኘ የኮርስ ክሬዲት እና<br>• የስነህይወት ሳይንስ ፈተና/ምዘና መውሰድ</td></tr>
</table>

[1]የማሟያ ፈተና፡- በማሟያ ፈተናዎች (AP/IB) ብቁ የሚያደርጋቸው ነጥቦችን ያገኙ ተማሪዎች በዚያ ይዘት የ MCAP HSA መስፈርትን ያሟላሉ።
[2]የተዛወረ ክሬዲት፡- ከሜሪላንድ ፐብሊክ ስኩልስ ውጪ በዝውውር የሚመጡ ተማሪዎች አንዳንድ የ MCAP HSA መስፈርቶችን ሲዛወሩ ባላቸው ክሬዲት ማሟላት ይችሉ ይሆናል።
[3]በ 2019–2020 ወይም 2020–2021 የኮቪድ መስፈርት እንዲታለፍ ተደርጓል።